ሚዛናዊነት - በኛ እና በሌሎች መነጻጸል

ዛሬ ላይ የብዙዎቻችን ችግር በሁሉም ጎናችን ማለትም በመንፈሳዊም ሆነ በዓለማዊ ጉዳዮች እኔ ነኝ ትከከለኛውን አካሄድከ እየተከተልኩ ያለሁት ብለን ማሰባችን ይመስለኛል። እኔ ሞዴል ነኝ፣ እኔ ምሳሌ ነኝ፣ እኔ ሚዛናዊ ነኝ፣ እኔ ትከከል ነኝ፣ እኔ ስህተት የለብኝም... ማለት የብዙዎቻችን ባህሪ ሆኗል። ለዚህም ነው መጣባባት የከበደን። ኢስላም ሲነሳ ሁሉም ትከከለኛውን የኢስላም አስተምህሮ የተከተልኩት እኔ ነኝ ብሎ ያምናል። ባህሪ ሲነሳ ሁሉም የሱ ዐባይ ልዩ እንደሆነ አድርጎ ይመለከታል። ሚዛናዊነት ሲወሳም ሁሉም "ሚዛናዊ ማለት እኔ ነኝ" ብሎ ወደራሱ ይጠቁማል።

ሁሉም ማለት ይቻላል ባለው የዓለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ፍልስፍና ራሱን ትከከል አድርጎ ያቀርባል። በዓለማዊ ጉዳዮች ሜዳም ብዙ ሰዎች ራሳቸውን የትከከለኛ ነገሮች መለኪያ እንደሆኑ አድርገው ያስባሉ። አንድ ወዳጄ መኪና አያያዝም ሆነ አነዳድ "ከኔ ተማሩ" ይመጣደቅ እንደነበር አስታውሳለሁ፤ ሚዛናዊ እንደሆነ ያስባል። ሲነዳም የሚቀድሙትን ምንድነው እንዲህ የሚያንከለከላቸው? ብሎ ይነጫነጫል፤ ቀስ ብለው የሚሄዱትን ደግሞ በቀርፋፋነታቸው ይተቻል። ሌላው ወዳጄ ደግሞ ገንዘብ ኢያያዝ ማለት እንደኔ ነው ይላል፤ ገንዘብ እየበተነ የርሱ አቋም ትከከል እንደሆነ የሚያስብ አለ። እየቋጠረም ትከከል ነኝ ብሎ የሚኮፈስ አለ። ሌላው ደግሞ ትዳር በዚህ መልኩ ነው መንኖር ያለበት ብሎ ይከራከራል፣ ሚስቱን እየበደለ ሴትን መያዝ እንዲህ ነው ብሎ ይከራከራል። ሌላው የሱ ባህሪ ፍፁም እንደሆነ አድርጎ ይመጣደቃል። ነጭናጫ መሆኑን አያስተውልም፤ ተናዳጅ መሆኑን አይገነዘብም።

በመንፈሳዊው ሕይወታችንም ብዙዎቻችን ትከከለኞቹ እኛ ነን ብለን እናስባለን። አንዳንዱ የሌሎችን ዒባዳ ጥያቄ ውስጥ ይከታል። ከሱ በዒባዳ የበለጡትን ሲያይ ሞኝነትና ዝም ብሎ ድካም እንደሆነ አድርጎ ያስባል። ከኔ ያንሳል ብሎ ያሰባቸውን ደግሞ ጅነት ከነርሱ እሩቅ እንደሆነ አድርጎ ያያል። ሌላው ደግሞ ለዒባዳዎች ግድ የሌለው አለ። ዋናው ቀልብ ነው በማለት በቀልቡ ንጽሕና ይኩራራል፤ ራሱን ከሌሎች የተለየ ፍፁም አድርጎ ያቀርባል፤ ሲፈልግም የሻውን ኃጢኣት ይሠራል፤ በዚህም የተነሳ ለአምልኮ ተግባራት ትኩረት መስጠትን፣ ሐላልና ሐራምን... ችላ ብሎታል። ስንመፀውት፣ ስንስቅ፣ ስንጫወት፣ ስናወራ ... ብዙዎቻችን የኛ አካሄድ ትከከል ነው ብለን እናስባለን። ራሳችንን ልኬትና መመዘኛ እናደርጋለን። ሰዎችም በዚሁ መስመር ቢጓዙ እንመኛለን፤ በዚሁ መርህ እንዲኖሩ እንፈልጋለን፤ እንመከራለንም።

ይመስለናል... ትልቁ ችግራችን ምን መሠላችሁ? ሚባዳዎችን ቆርጠን፣ የአምልኮ ተግባራትን ግማሹን ይዘን ግማሹን ጥለን፣ ሥነምግባራትን አንሻፈንና አጣመን ተረድተን... ያለንበት ነገር ሁሉ ልክ እና ፍፁም ይመስለናል። ቶሎ ቶሎ የመቆጣት ባህሪያችን ቆም ተብሎ ቢገመገም ትክክል እንዳልሆነ እየታወቀ ትክክል ይመስለናል፤ ቸልተኝነታችን ስንፍና እንደሆነ ግልጽ ቢሆንም ለኛ ግን ጉበዝና ሆኖ ይጠዘጥብናል። የጅማዓ ሶላት ብናረፍድ፣ የሶላት ሱንና ባንሰግድ፣ የሱንና ፆሞችን ባንፆም፣ እውነታውን ሳናውቅ ብንከራከር ... ትክክል የሆንን ይመስለናል። በትክክል ቢመዘኑ ስህተት እንደሆኑ ሊታወቁ የሚችሉ ሽሽቶታችን፣ ድፍረቶታችን፣ ፍርሃቶቻችን፣ ንግግሮቻችን፣ ዝምታዎቻችን... ሁሉ ትክክል ይመስሉናል። ትክክል መምሰል ብቻ ኢይደለም ትክክል የሚሠሩትን ሰዎች ስናጣጥል ይታያል። ሰዎች 'የኛ ዓይነት' ካልሆኑ ከመንገድ የወጡ ይመስለናል። ትክክል ናቸው የምንላቸው በኑሮም ሆነ ከሰዎች ጋር ባላቸው መስተጋብር የኛን ዓይነት አካሄድ የመረጡ እንደሆነ ነው። የኛ ዓይነት ፈገግታና የኛ ዓይነት ቁጣ ማሳየት አለባቸው። በኛ እይታ ምጽዋታችን፣ ሶላታችን፣ ዚክራችን፣... ደረጃውን የጠበቀና ሚዛናዊ ነው።

በጊዜ ወደ መስጂድ የሚሄድ፣ ሱንና ጨማምሮ የሚሰግድና የሚፆም ሰው ትክክል ላይመስለን ሁሉ ይችላል። ዛሬ ላይ ትክክል የመሰሉን ነገሮች ኋላ ላይ የመጡ ናቸው። ብዙዎቹ ደግሞ በስንፍናችንና በድክመታችን ምክንያት መንገድ አድርገን የያዝናቸው ነገሮች ናቸው።

በዚህ ሩጫና ግርግር በበዛበት ዓለም ቆም ብሎ ራስንን መመልከትና ከራሰ ጋር እውነተኛ መሆንን የመሰለ ነገር የለም። ከሚሮጡት ጋር ዝምብሎ የመሮጥ የረጅም ጊዜ ልምዳችንን ገታ ማድረግ በየጊዜው ራሳችንን መፈተሽ ይኖርብናል። እንደማንኛውም ነገር ሁሉ የሰው ልጅም ሃሳቡና አመለካከቱ በየጊዜው ከለሳና እድሳት ያስፈልገዋል ብዬ አስባለሁ። ለዘመናት የኖርንበት፣ ሙጭጭ ያልንበት ፀባያችን በርግጥም ጥሩ ስለመሆኑ እንደገና መገምገም አለበት። አቋም ይዘን የተከራከርንበት ጉዳይ በርግጥም ትክክል ስለመሆኑ ጊዜ ተሠጥቶ መጠናት አለበት። በግምገማና በጥናት፣ በጥሞናና በማስተንተን፣ ከእውነት ይደረሳልና፤ አብዝቶ ይተረፋልና። ይህ ሁሉ መደረግ ያለበት ራሳችንን ለማሻሻልና የተሻለ ሰው ለመሆን ነው። የተሻለ ሰው መሆንን የሚያልም ሰው፣ የንግድ አሠራሩን በየጊዜው እንደሚያሻሽለውና እንደሚከልሰው ነጋዴ ሁሉ ራሱንም ለማሻሻል መላ ሁኔታውን መገምገም አለበት ብዬ አስባለሁ።

ሁሌም አንድን ነገር ትከከል ነን ብለን ከማሰባችንም ሆነ ከመከራከራችን በፊት እውነታውን ማወቅ አለብን። እውነታው ከምናስበው በተቃራኒ መሆኑን ያወቅን እንደሆነ ደግሞ መራራም ቢሆን መቀበል ይኖርብናል።

መካከለኛነትና ሚዛናዊነት ኢስላማዊ አስተምህሮ ነው። በዲንያም ሆነ አኺራዊ ጉዳዮች ሚዛንን ጠብቆ መጓዝ፣ መካከለኛነትን መምረጥ ትልቅ የደስታ ምንጭ ነው። በተቻለን መጠን ሚዛናዊ እንሁን። ለሁሉም ነገር መለኪያው እኔ ነኝ ብሎ ማሰብ በራስ መደነቅ እና እቡይነት ነው። አላህ አይወደውም። ዘወትር ራሳችንን ቆም ብለን በጥልቀት የመመርመር ልማድ ይኑረን። የሰዎችን ጉዳይ ለራሳቸው እንተው። ስለ ራሳችን ብዙ እንጨነቅ። ራሳችንን እንገንባ። ማንነታችንን እናሻሽል። ጠንካራ ከሆንን አላህ ያዘልቅልን ዘንድ እንለምነው። ደካማ ከሆንን በየቀኑ ወደ አላህ እንቃረብ። ጉዳያችንን ያስተካከልልን ዘንድም እንማፀነው።

ማስታወሻ

የመሰተር ፀጋ

የምድር ላይ ትልቅ ዱዓኤ "አላህ ሆይ ሰትረኝ!" የሚለው ነው። አምላኬ ሆይ እርቃኔን ነኝና ሰትረኝ። ‹ሰትረኝ› ብዬ ሳልማፀን የዋልኩበት ቀን አለ ብዬ አላስታውስም፤ ሐልላሁም ስቱር ዐውራቲ፤ ወኣሚን ረውዓቲ›።

አላህ በእገዘነቱ ሰተረን እንጂ ቢያጋልጠን ኖሮ የያንዳንዳችን ስንት ጉዳችን በታየ!። ስንቱ ነውራችንም ይፋ በሆነ!።

መሰተር ከኃጢኣት ብቻ አይደለም ወዳጀቼ። አላስተዋልንም እንጂ አላህ በብዙ መልኩ ሰትሮናል።

- አብልቶ አጠጥቶ አውሎን ከረሃብ አለንጋ ሰተረን።
- ለገላችን መሸፈኛ ልብስ ሠጥቶን ከብርድ ውጋት ሰተረን።
- ጤናና ጥንካሬ ሰጥቶን በሰው እጅ ከመውደቅ እፍረት ሰተረን።
- መሳቅ መጫወትን ለግሶን ከሐዘን ስብራት ሰተረን።
- ጥሩ ወንድሞችና ጓደኞች ሰጥቶን ከባይተዋርነት ህመም ሰተረን።

- ማንበብና መረዳትን አስተምሮን ከመሃይምነት ጨለማ ሰተረን።
- የምንወዳቸው ቤተሰብና ልጆች ሰጥቶን ከብቸኝነት ሕይወት ሰተረን።
- ሥራና መዋያ ረዝቆን ከልመና ውርደት ሰተረን።
- አገርና ቤት ሰጥቶን ከስደት ግርፋት ሰተረን።
- አስልምናን ሰጥቶን ከማያባራ የነፍስ ሥጋ ጥያቄ ሰተረን።

መሰተር ትልቅ ፀጋ ነው። የአላህ ሲትር አይለያችሁ። አላህን ጤና እና ሲትር ለምኑት።

ኸልዋ - ከአላህ ጋር የመሆን ድባብ

አላህ (ሱ.ወ.) የዱንያ ላይ ሕይወትን አንድ ዓይነት ብቻ አላደረጋትም። ብዙ ዓይነትና መንገድ አድርጎ አበጃት። ዓይነቷ መብዛቱ በተፈጥሮና በባህሪው ስልቹ ለሆነው ለሰው ልጅ ትልቅ ጥቅም ነው። ከቢፈዎቿ እየመረጠ ይወስዳል። ሰንኖር ሁሌ ከሰው መቀላቀልና መጫወት፣ ማውራትና ማውጋት ላያምረን ይችላል። አንዳንዴ ኸልዋ ያምረናል። ብቸኝነት ይናፍቀናል። በርግጥም በብቸኝነት ዓለም ውስጥ ብቻ እንጂ ሊፈቱና ሊተረጎሙ የማይችሉ የሕይወት እንቆቅልሾች አሉን።

ኸልዋ ማለት መገለል ነው፤ በሆነ ምክንያት ለብቻ መሆንን መፈለግ። ዱንያ ብራ ብቻ አይደለችም፤ ጭጋግም አላት። አንዳንድ ጊዜ እንዲሁ የሚጫነን ነገር ይኖራል። ሁሌም በጥሩ ኢማን አንዘልቅም፤ አንዳንዴ ይደክመናል። ኢማናችንን ሲወርድ ያሳስበናል። በዚህ ጊዜ ድባቡን መቀየር ያስፈልጋል። ሁኔታችን ደስ ሳይለን ሲቀር፣ ሲደብረን፣ ሐዘን ሲወርሰን፣ ሃሳብ ሲገባን፣ ሲጨንቀን... ብዙዎቻችን ብቸኝነትን እንመርጣለን። በዚህ ዓይነቱ ጊዜ ከሰዎች ለመራቅ ብለን ወጣ እንላለን፤ አሊያም 'ወከ' እናደርጋለን፤ ወይም ወደ ባህር ዳርቻና ፀጥ ወዳለ ሥፍራ እንሄዳለን። ወይም ደግሞ ብቻችንን ስልካችንን ዘግተን፣ ድምጣችንን አጥፍተን ቤት ውስጥ ብቻችንን እንሆናለን። ጫጫታ ሲበዛብን፣ ሁካታና ግርግር ሲደራረብብን... ለብቻ መሆንን ነፍሳችን ትሻለች። ሰው ማግኘትም ሆነ ከሰው ጋር ማውራት ያስጠላናል።

የዚህ ዓይነቱ ስሜት በሽታ አሊያም መጥፎ ባህሪ አይደለም። ስለሆነም ብቸኝነትን የሚመርጥ ሰውም በደፈናው መተቸት የለበትም። ምክንያቱ ሊታወቅለት ይገባል። ከሰዎች ጋር ከመቀላቀል ይልቅ በመገለሉ ጥሩ ውጤት አግኝቶበት ሊሆን ይችላልና። በርግጥም ከመጥፎ ጓደኛ እና በጎ ካልሆነ ስብስብ ብቸኝነት ይመረጣል። ከመናገር ይልቅ ዝምታ የሚበልጥበት አጋጣሚም አለ።

ኸልዋ ውስጣችንን ለማዳመጥና ለራሳችን ጊዜ ለመስጠት ከምንጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው። ራሳችንን ለማደስ፣ ድከመታችንን ለማረምና የበለጠ ለመጠንከር እንጠቀምበታለን። አንዳንድ ጊዜ በዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ እንጂ ሊመለሱ የማይመለሱ ጥያቄዎች ይኖሩናል። ተገልለን ከራሳችን ጋር ስናወራ፣ ራሳችንን ስንገመግም፣ ከራሳችን ጋር ብቻ ለብቻ ስንሆን፣ ውስጣችንን ስናዳምጥ ይመለሱልናል።

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማኅበራዊ ነው፤ ሰው ያስፈልገዋል። አባታችን አደም (ዐ.ሰ.) እንኳን በዚያ ያ ሁሉ ተድላና ፀጋ በሞላበት የጀነት ዓለም ብቻቸውን አልኖሩም። ሰው

ስላስፈለጋቸው አላህ (ሱ.ወ.) ሐዋን ሠጣቸው። የዱንያ ሕይወት ትሠለቻለች። የሰው ልጅ በአንድ ነገርና ስሜት ላይ አይረጋም። ስሜታችን እንደ አየር ፀባይ ሁሉ ተለዋዋጭ ነው። ብቸኝነት ሲበዛ ከሰው መቀላቀል... ከሰው መቀላቀል ሲበዛ ብቸኝነትን መምረጥ፣ በጥሩ መንፈስ ለመቆየት አንዱ የኑሮ ስልት ነው። ስለዚህ አንዳንዴ ኸልዋ ግድ ነው። ኸልዋ የተመስጦ ዓለም ነው። ወደ ሰማዩ ዓለም ከፍ ለማለት፣ ወደፊት ለመንደርደር እና ለመሰፈንጠር ተጨማሪ ኃይል እና ጉልበት የሚሆንበት አጋጣሚም አለ።

ኸልዋ ለዚክር፣ ለዒባዳ እና ተገልሎ ወደ አላህ (ሱ.ወ.) ለማልቀስ ብቻ አይደለም አስፈላጊነቱ። በዱንያ ሩጫዎች መሃል ቆሞ ብሎ ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅና ራስን ለመገምገም፤ ከግምገማ በኋላም ጥሩ ውጤት ይዞ ለመውጣት ኸልዋ አስፈላጊ ነው።

ከአላህ ጋር ተገልለው ለብቻ ሲሆኑ፣ ኸልዋ መደበቅ ሳይሆን ጎልቶ መታየት ነው፤ መጥፋት ሳይሆን መኖር ነው፤ ወደ አላህ መቅረብ ነው። ጌታዬ ሆይ! እየኝ እዚህ ነኝ ማለት ነው። ለሐኪም እንደሚደረገውና ሁሉ ነገር በግልጽ እንደሚነገረው፤ አልትራሳውንድ ፊት በሽታን ለመፈተሽ ራቁት እንደሚቀረበው ሁሉ፣ አላህ ፊት በመቅረብ ሁሉን ገላልጦ ማሳያ ቦታ ነው -ኸልዋ።

በኸልዋ ጎጆ ውስጥ ዱዓ ይደረጋል። ትኩስ እንባ ይፈሳል። ሁሉ ብሥት ይዘረገፋል። አንድም ነገር ሳይቀር ለአላህ ይነገራል። ዱዓ በችግር ጊዜ ብቻ የምንናገርበት መድረክ፣ ጥቅምን ብቻ የምናሳድድበት ነፃ መስመር አይደለም። ከልብ የሆነ ዱዓ ሲደረግ በይድረስ ይድረስ መልኩ አይደረግም፤ ያለህንና የያዝከውን አራግፈህ ቶሎ አትሮጥም። ባይሆን የፍቅር አምላክ ለሆነው ጌታ ጉዳይህን ታቀርባለህ። የፍቅር ውይይት ታደርጋለህ። ታንሾካሹካለህ። ዱዓ በአዛኝ እና ታዛኝ፣ በሃብታምና ድሃ፣ በፈጣሪና ፍጡር፣ ሁሉን ባለው እና ምንም በሌለው፣ ሁሉን ማድረግ በሚችል ኃያል እና ምንም ማድረግ በማይችል ደካማ መካከል የሚደረግ ሚስጥር ነው። በዚያ ቦታ ላይ ከትንሽ እስከ ትልቅ ምንም የምትደብቀው ጉዳይ፤ አንድም የምታፍርበት ነገር አይኖርም። ኸልዋ ያቆርነው እንባ ግድቡን የሚደረምስበት ጓዳ ነው። ያደከመንን፣ ያሳሰበንን፣ መሸከም ያቃተንን ኮተት ሁሉ የምናራግፈበት ሜዳ ነው።

በትኩረት ዱዓ ለማድረግ፣ በተመስጦ አላህን ለማውሳትም ሆነ ቁርአን ለመቅራት፣ በልዩ ሁኔታ ከአላህ ጋር ለመሆን አንዳንድ ኸልዋ ያስፈልጋልና እንጠቀምበት።